# መንፈሱ አልበጀ ውቃቢው ሰው ፈጀ

በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ለዴሞክራሲ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር እንታገላለን የሚሉ የተለያዩ ተቋዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። አንዳንዶቹ በገዢው መንግስት የበረታ ግልምጫ ያላዩ መሆናቸው አያከራክርም። ተቋዋሚ ድርጅቶች ይብዛም ይነስም እንወክለዋለን የሚሉት ሕዝብ አለ። ሕዝቡ ግፍና ሰቆቃ አብቅቶ የተሻለ ዘመን ያመጡለት ዘንዳ ይጠብቃል። የፖለቲካ ትግል ፍሬውን ለመቅመስ የሚጠይቀው መስዋዕትነት ከፍተኛ ነው። በደም ዋጋ የሚገነባና የሚለሰን ነውና በልመናና ደጅ በመጥናት በዋል ፈሰስ በሆታና አንዱ ሌላውን በመኮነን በቁራ ጩኸትም የሚመጣ አይደለም።

ዛሬ አገራችንና ወገናችን ለወደቁበት የፖለቲካ የኢኮኖሚ የማህበራዊና ስነልቡናዊ ዳፋና ለመከፋፈላችን የራሳችን የመደማመጥና የመቻቻል ችግሮች እንዳሉ ሁነው ባዕድም ጣልቃ እየገባባቸው ወይንም የራሱን አጀንዳና ዕቅድ እያስታቀፈን ወገናችን ከድጡ ወደ ማጡ ከሳቱ ወደ ረመጡ እየተማገደ ይገኛል። የግፍና የሰቆቃ መንሰኤውን ከወዲሁ በውል አጢኖ ኢትዮጵያዊ ባህል ወግና ስነ ምግባር ፈፅሞውን ሳይጠፋ መዋጋት ያለብን ኢትዮጵያዊነትን ሳይሆን ጎጠኝነትን አንድነትን ሳይሆን መከፋፈልን ሊሆን ይገባል። መጎልበት ያለበት ባዕድ ደጅ መጥናትን ሳይሆን በሕዝባችንና በወገናችን ላይ መተማመን ነው። አሊያ ለአገር በቀልና ለባዕድ ጠላት መሣሪያ ከመሆን ያለፍን አንሆንም። ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንባው ቂጥጥ እንዳይሆንም ገና ለመንግሥት ሥልጣን ሳይበቃ ርስ በራስ መሻኮትንና መናቆርን የድርጅት ውስጥ ትግልና የሥልጣን ሽሚያ ወደ ጎን አድርጎ ከራስ ዝናና ከድርጅት ስም በላይ የአገርና የወገንን ልቅሶና ዋይታ አዳምጦ ወዳጅና ጠላትንም ለይቶ አደብ መግዛቱ ይበጃል።

በኢሕአፓ ላይስ ለምን ጩኸት በረከተ ዘመቾቹና አዝማቾቹስ እነማን ናቸው? ለመሆኑ ኢሕአፓን የሚከሱና የሚኮንኑት ለምንድን ነው? ብለን መጠየቁ ተገቢ ነው። ኢሕአፓን የሚከሱና የሚኮንኑት 1ኛ. የደርግ ኢሰፓ ነፍሰ ገዳዮች 2ኛ. በተለያየ ጊዜ ከኢሕአፓ የከዱ ወደ ደርግ ኢሰፓና ወያኔ ኢህአዴግ ወዶ ገባዎች 3ኛ. ጠባብ ብሔርተኞችና ጎጠኞች 4ኛ ግዙፉ የነቃው ኃይል(the awakening giants) ነን የሚሉት ናቸው።

በደርግ ኢሠፓ ዘመን በቀይ ሽብርና በተለያዩ ጊዜያት በኢሕአፓ አባላት በተለይ በወጣቱ ላይ የግፍ ግፍ ሲፈጽሙና የቁም ስቅል ሲያሳዩ የነበሩ በእጃቸው የገቡ ሴቶችን በስካር መንፈስ በሌሊት እያወጡ ለመድፈር ሲሞክሩ እምቢኝ አሻፈረኝ እያሉ ሲተፉባቸው ወንድነታቸው እየከዳቸው በጉልበት መድፈርም ስያቅታቸው ማህፀንን ብልትንና ጡትን ስሡና ክቡር ነገር በጋለ ብረት እየጠበሱ ጥፍርን በፈላ ዘይት እያነፈሩ በጉጠት የሚነቅሉ የወንድ ብልትን እንደ ኮርማ በሬ እየቀጥቀጡ የዓይን ብሌን በሲጋራ ፍም እያቃጠሉ ሲያጠፉ የነበሩ የገዛ ወላጅ እናቶቻቸውን በታጠቁት ሽጉጥ ሰደፍ የሚደበድቡ™ ኢሕአፓን ጨርሰናል አልቆለታል ˜ብለው

ለመረጋጋት ቢሞክሩም የንፁሃን ደም የሰማዕታት ደም እያሳደዳቸውና እንቅልፍ እየነሳቸው ኮሽ ባለ ቁጥር በፍርሃት ሰቀቀን የሚባንኑ ወዳጅ ዘመድ ወግድልኝ ያላቸው የደርግ ኢሰፓ ነፍስ ገዳዮችና ባንዳዎች ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት ኢሕአፓ አናርኪስት መንግሥት የተባለን የሚጠላ አስገንጣይ ቶወዘተ ሲሉ የነበሩ ግማሽ ሚሊያን ወታደር የስንት ቢሊየን ዶላር የጦር መሣሪያ ይዘው መዋጋትና ማዋጋት ተስኖአቸው ርስ በራስ ሲሻኮቱ ሠራዊታቸውን በሴት በውስኪ በጮማና በሐሰት ዶላር የሸጡ የሞተና የከዳን እያወቁ በጊዜው ለቤተሰብ የመርዶ ዜና በማድረስና ተገቢውንም ወሮታ ለቤተሰቦቻቸው በመክፈል ፈንታ በሕይወት እንዳሉ አስቆጥረው ምንዳቸውን እያወጡ የደም ዋጋን የበሉና ወላጅንም እርም ያስበሉ በቅናትና በምቀኝነት መተኪያ የሌላቸውን የአገር መከታም የሆኑ አዛዦቻቸውን አንገት የቀረጡና ያስቀረጡ ዘመናዊ ጦር አስደምሠው የኀበዝ አለቃ ያለህ ብልርው የለመኑ የዘሩትን ያጨዱ ከሕዝቡ በግርግር የነጠቁትን ሥልጣን የተቀሙ ሠራዊታቸውን በትነው ወደ ስደት ያቀጠኑ ደባና ሴራቸውን ኢሕአፓ ጠንቅቆ ያውቃልና ጆሮ አይሰጣቸውም።፡ ዛሬ ደርሰው የዚህ ግንባር የዚያ ግንባር እያሉ በሕዝብ ልጆች ደም የሚቀልዱ ኢሕአፓ አሰናከለን ይሉናል። ቁርበት አንጥፉልን እያሉ እንዳይመፃደቁም ኢሕአፓ የቀን ጅቦች ናቸው ስለሚላቸው አይመቻቸውም። ለፈፀሙትና ላስፈፀሙት ዛሬም ለሚፈፅሙት ኢ-ሰባዓዊ ተግባርም ፀፀት የማይሰማቸው የአዕምሮ በሽተኞች(psychopaths) ናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብም በቀለኛና ቂመኛ ቢሆን ኑሮ ወያኔ ኢህአዴግ አፈርሳታና አውጫጭኝ አመቻችቶ ለበቀል በተዘጋጀበት ጊዜና የሕዝቡን ይሁንታ በጠበቀበት ሰዓት አጋጣሚውን መጠቀም ይቻል ነበር። በእነዚህ በየከተማውና በየቀበሌው በተዘጋጁ የአፈርሳታና የአውጫጭኝ ስብሰባዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉትን የደርግ ኢሠፓ ካድሬዎችና ሹም ባሾች በአደባባይ ሲያናዝዙ ሕዝቡ በአግርሞት ተመለከተ እንጂ ትላንት ለተፈፀመበት ሰቆቃና ግፍ ተበቀልሉኝ አላለም ። ምህረት አደረግሁም ይደረግም አላለም ዝም እንጂ። ፍትህ ሰጪ ነኝ ባዩ ራሱ እጁን በደም የታጠበና የሞራል ብቃትም የሌለው በመሆኑ ነው። ዛዲያ እነዚህ ነፈሰ ገዳዮች የኢትዮጵያን ሕዝብ ወሮታ የሚከፍሉት አስተዋይነቱን ከድንቁርና ቆጥረው በባዕድ በስደት የሚንከራተተውን ሕዝባዊ ወገን እየከፋፈሉትና እያመሱት ነው።

2. በአንድ ወቅት በኢሕአፓ ሥር ተደራጅተው ለምልዓተ ሕዝቡ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፍትህ እንታገላለን እያሉ ሲምሉና ሲገዘቱ የነበሩና የፖለቲካ ወግ አይቀር እንዲሉ የመስመር ልዩነት አለን ብለው ሃሳባቸውን በቅጡ ማስረገጥ ያልቻሉ ለወትሮውም ሚናቸው ከጥራዝ ነጠቅነት ያልዘለቀ የድርጅታቸውን ልሳን እንኳን በቅጡ አንብበው የማይጨርሱ ትግሉ በሜዳም ይሁን በከተማ የጠየቀውን መስዋትነት ረሃብ ጥማት መቋቋም ሲያቅታቸው ˜ትግል አያስፈልግም። አይቻልም። በመርፌ የተወጋች አንዲት ጠብታም ብትሆን መፍሰስ የለባትም™ በማለት ገና ትግሉ ከመክረሩና እየመረረም ከመምጣቱ በፊት ማጭድና መዶሻ ንቀሱንና አራዳ እንውጣ ፋሺዝም ይውደም እንዳላሉ በውሾ ሆድ ቅቤ ውሎ አያድርምና በተለይ ከበለሳው የኢሕአሠ ኃይል ለመክዳት ሲሞክሩ ሲያደራጁትና ብሩህ ተስፋ ሲሉት በነበረው አርሶ አደር

ተከበው የተያዙ በኃላም መሣሪያቸውን እየተቀበለ ˜በድርጅትችሁ ደንብ መሰረት አንታገልም ብትሉ መሰናበት የምትችሉ መሆኑን እናውቃለን መሣሪያው ግን የሕዝብ ነው ˜ በማለት ትጥቃቸውን እያስፈታ የለቀቃቸው ከዚያ ከበባ ቀንቶአቸው የወጡ ገሚሱ ለስደት ወደ ሱዳን ከፊሉ ደግሞ ከወያኔ ለማደር ሲጠጋ ገሚሱ ደግሞ ተከዜ ለሚገኘው የደርግ ጦር እጅ በመስጠት መጠጊያ የሰጡአቸውን አርሶ አደሮችና በድርጅቱ ላይም ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ የሚያውቁአቸውን የኢሕአፓ አባላትንና ደጋፊዎች የጠቆሙ የገረፉና ያስገረፉ ያስገደሉም አንጃና ከሃዲዎች ናቸው።

እነዚህ በሁለተኛው ረድፍ የተቀመጡቱት ገሚሱ ˜ኢሕአፓ ስህተት ሠራ ወጣቱን አስጨረሰ™ የሚሉ ከሕብረ ብሔርነትም ወርደው ወደ ጎጠኝነት የዘቀጡ ድል አድርገን ገባን ቢሉ እንኳን ጉሮ ወሸባዬ ያልተባለለቸው  የወያኔ ጎጥ ቡሃቃ ከነሊጡ ተሸካሚዎች የጎጠኛ ድርጅቶችን እየኮለኮሉ (‡ ዴድንና ... ዴንን ያጤኑዋል) ሕዝቡን ግራ ለማጋባት ሞክረው ሳይሳካላቸው ሲቀር ሕዝቡ ቀድሞአቸው ነቅቶ ኑሮ በዘር አትቀስቅሱኝ  ብሎ አምርሮ ሲታገላቸው ኢሕአፓ ቀሰቀሰብን ይላሉ። ጠፍታል ያሉትንም ኢሕአፓን ይከሳሉ።

በ1981 ፎረም 84 በሚል የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት ስብሰባ በሚል በዳግማዊ ምንሊክ በተፈሪ መኮንን በኢትዮጵያ መብራት ኃይል የስብሰባ አዳራሾች ተከታታይ ስብሰባዎችን እየጠሩ የኢሕአፓን አለመኖር ሊያስረግጡ ቢሞክሩ በተለይም ሁልጊዜ የማወቅ ጉጉት ያለው የወጣቱ ክፍል አላስዋሸ ብሎ በጥያቄ ወጥሮ ሲይዛቸው ˜ ሐቀኛ ኢሕአፓዎች እኛ ነን እኛ የኤሕአፓ ተወካዮች ነን እነርሱ ቡርዣ ሆነዋል ትግል አብቅተዋል™ እያሉ ሊያደናግሩ ቢሞክሩም ሳይሳካላቸው ሲቀር ወዲያው በሌላ መድረክ ብቅ ብለው ደግሞ እነርሱ ˜ጦረኞች ናቸው። ጦርነት አውጀዋል የጦር አዋጃቸውን ካነሱ በሽግግሩ ሊሳተፉ ይችላሉ™ እያሉ ሲያደነቁሩን ነበር። ልብ በሉ በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ እንዳይካፈሉ የተደረገው ጦር የላቸውም በሚል ነበር ። ዛዲያ የለም ያሉት ኢሕአፓ ከዬት መጣ? ˜እውነትም ለምን አይገቡም እንደሚባለው አልቆለት ይሆን?™ ብለው ለተጠራጠሩትም በአውሮጳ የኢሕአፓ(ኢዴሃቅ) ተወካይ ጋዲት ገነት ግርማ በቦሌ ብትገባ ሄርኩሉስ ጦር ይዛ የገባችባቸው ይመስል አንጀኛና ከሃዲ ባንዳ ሁሉ ምን ያህል በፍርሃት ብብቱ መከርፋት እንደጀመረ ታዝበን ያለፍነው ነበር።

3. ገና ከጅምሩ ሲፈጠሩና ሲጠነሰሱ የምልዓተ ሕዝቡን ይሁንታ ያላገኙ ኢሕአፓ የታገላቸውና ዛሬም የሚታገላቸው ቆመነልሃል ነፃ እናወጣሃለን ያሉትን ሕዝብ በለስ ቀንቶቸውና  በባዕድ ርዳታ ተደግፈው የመንግሥት ሥልጣን ቢይዙ ገሚሶቹም ሥልጣን ቢካፈሉ ነፃ አወጣንህ ያሉትን ሕዝብ በብረት ዘንግ የሚገዙ አምባገነኖች ወከልንህ ያሉትንም ሕዝብ አምባገነን አንግሰውበት™ ሕዝባቸውንም™ ለወያኔ ኢሀአዴግ የቀን ጅቦች ጥለው የፈረጠጡ በሺ የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችን በምዕራብ ሐረርጌ ከአሰቦት አንስቶ እስከ ዝግታ ያስጨፈጨፉ በምዕራብ ኢትዮጵያ ከአሰንዳቦ አንስቶ እስከ ሲግሞ ሰጠማ  የተከተሉአቸውን

አርሶአደሮችና  የመንግሥት ሠራተኞች ለስደት ለእስርና ለእንግልት የዳረጉ በስማቸውም ቤት ንብረቱን ጥሎ በገዛ አገሩ ውስጥ ለሚንከራተተው በሱዳን በጋዳሪፍ በኬኒያ በካኩማ በሱማሌ በቦሶሶ፣ወዘተ በስደት ለሚንገላታው ቁብና ደንታ የሌላቸው ˜ነፃ አውጪ ነን™ ባዮችም ሊገፉን የማያደርጉት ደባ የለም።  እንደ ደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪም አስመራ ላይ በዕዳ ታገቱ ሲባል የምንሰማበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ጠባብ ብሔርተኞችና ጎጠኞች ከመሠረታቸው ˜ ማርክሳዊ ነን™ ብለው በብሔር ጥያቄ ዙሪያም ተራቀናል ቢሉም ትንተናቸው ከአፍንጫቸው ያልራቀና የዳበሳ መሆኑን ለመሸፈን አንዴ ˜ትምክህተኛ™ ሌላ ጊዜ ደግሞ ˜አክራሪ™ እያሉ ገበናቸውን አጋላጭ የሆነውን ኢሕአፓን ይከሳሉ። የዘር ጥላቻንም መሠረት ያደረጉና ትውልድና ትውልድንም በመከፋፈል ያለፈውንም ታሪክና የጠገገ ቁስል ጠባሳ እየላጡና እያመረቀዙ ራሳቸውንም በታሪክና በሕዝብ ፊንታ ተክተው ዓቃቤ ከሳሽ በያን ዳኛም ይሆናሉ። ጠባብ ብሔርተኞች ዶሮ ብታልም ጥሬዋን እንዲሉ መሠረታቸው ዘር አጀንዳቸውም ጎጠኝነት ነው። የአምባገነኖች መሣሪያዎች የነበሩ ያሉና ወደ ፊትም የሚሆኑ ብቻ ናቸው። ባለፈው ትውልድ ላይ የያዙትን ቂምና ጥላቻ አቅፈውና አንግበው ለታሪክ ፍርድ መተው የሚገባውን ጊዜን  የኃሊት ወስዶ ጥላቻን መዝራት መለያ የፖለቲካ ስንቃቸው ያደረጉ ሕዝቡ አበክሮ በጋራ እንዳይታገል በጎጥ እየከፈሉት የቆቅና የግፍ ዘመኑን ያራዝሙበታል።

ሕዝባዊነታቸውን ግን  በነፃ እንዲታደል በርዳታ የመጣ የመድኃኒት ˜የጦር ብዝበዛችን ነው ዋጋውንም  ክፈሉን™ ብለው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን አስገድደው ገንዘብ የሚቀበሉ ንፉጎች አዛውንትንና ሕፃናትን በአደባበይ መግደልን ርጉዝ በሣንጃ ነድሎ ሽል ማውጣትንና ማረድን ከገደል መጣልን ራስን በራስ ማስተዳደርና ዴሞክራሲ ነው ይሉናል። በኃይል በውሸትና በማታለልም የሕዝብ ልብ የሚገዛ ይመስላቸዋል። እምቢ ሕዝቡ አልገዛም ሲላቸው ያበሳጫቸዋል። ልትበተንም ነው ሲሉ በሟርት ያስፈራሩታል። በቀን ሦስቴ ትበላለህ ያሉትንም ሕዝብ እነርሱ ጠግበው እያገሱበት በቀን አንዴ እንኳን ነስተውት ያስርቡታል። ዕዳ እየጫኑበትም ክብርም ነፍገውት እምባገነን በመሆን ይዘባበቱበታል ። ይሳለቁበታል።

4. የመጨረሻዎቹ የነቃው ግዙፍ ኃይል ነን የሚሉቱ ለፎቶና ቪዲዮ ካሜራ ጠብ ርግፍ የሚሉ መድረካቸውን በኢትዮጵያ ባንዲራ የሚያጌጡ ግብዞች ሸንጎአቸው ሲያበቃም ያጌጡበትን ባንዲራ በፖለቲካ መሸታቸው አሳድፈው በየስርቻው ወትፈው ዘር የሚሉ ዛሬ እየደረሰና ላለው ዳፋ የተማሪውን ንቅናቄ ግራነት የሚኮንኑ ደርሶ እነርሱ የረቡብሊካንና የሊበራል ፖለቲካ አመለካከት አራማጆች ነበርን ለማለት የሚዳዳቸው ኢሕአፓን ግራ ነው ይሉታል ። ዛሬም አርሶአደር ላብ አደር ይላል ብለውም ይከሱታል። ራዕይ አየንልህ የሚሉት ሕዝብ ማንና ዬቱን ይሆን? ክሳቸው ሰሚ ያጣ ጩኸት ነው። ኢሕአፓ መች ቀኝ ነኝ አለ ቀኙን እናንተ ተገፋፉበት። ተጠላለፉበት። ክቡር ክቡር ክብርት ክብርት ተባባሉበት። ኢሕአፓ

ግፊያ ባልበዛበት ከምንዱባን ጎራ ውሎ ቢያድር ዛሬም አይገደውም። ምልዓተ ሕዝቡ የሚላቸው እነርሱ ናቸውና።

ወጣቱ በኢሕአፓ ሥር ተደራጅቶ ፊውዳሊዝምንና ፋሺዝምን ሲዋጋ የቀ.ኃ.ሥ ወጣት ድርጅት አባላት የነበሩ የተለያዩ የባዕድ ሃይማኖት ቤተክርስቲያናትንና የአሜሪካንን የባህል እንፎርሜሽን ማዕከል በአዲስ አበባ የሚያዘወትሩ የነበሩ ፖለቲካና ኮሬንቲ በሩቁ ነው በማለት በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የግል ሕይወታቸውን ሲያደራጁ የቆዩ ባዕዳንን በምርምርና በጥናት ዞግ እያደረጉ የሕዝቡን ገበናና የአገርንም ምስጢር የሚያዘረክርኩ ወያኔ ኢህአዴግን በመለማመጥ አሊያም ሕዝባቸውን ሳይሆን ባዕዳንን አማላጅና ተገን  በማድረግ በቅድመ ኢህአደግ ባዕዳን የሥልጣን ልጨኛ ብለው ያደራጁአቸው በኃላም ጦር የላቸውም ተብለው የተናቁ ዛሬ ደግሞ ወያኔ ቢወድቅ ባዕድ ጥቅሜን ሊያስከብሩኝ ይችሉ ይሆናል በሚል እያዘጋጃቸው ያሉ የሥልጣን ክፍተት ቢፈጠር በሚል ተኝተው የማያድሩ ባልዋሉበት ዐውደ ፍልሚያ ራሳቸውን በኢትዮጵያ ጉዳይ ጠቢብና ሊቅ አድርገው የወገናቸውን ብቃትና ንቃት በመናቅ እኛ እናውቅልሃለን አንተ ብቻ ተከተለን የሚሉ ሕዝቡ የቀደማቸው ሊቅነትን ተጭነናል ብለው የሚኮፈሱ መጅ የሌለው ወፍጮዎች ናቸው፡፡

ሥልጣኔ ባዘመነው ዓለም ውስጥ እየኖሩ ድፍን ሠላሳ ዓመታት ድምፃቸውን አጥፍተው ኖረው ራሳቸውን የነቃው ግዙፍ ኃይል ነን በማለት ደርሶ ፀረ ኮሚኒስት ረፑብሊካንና ሊበራል አመለካከት አቀንቃኝ ነን የሚሉ በባዕድ ከተሞች የዚህ ሊግ የዚያ ቻፕተር እያሉ የሚሻሻሙ በድርጅት ላይ ድርጅት የሚደርቱ ርስ በራሳቸው እንኳን ለመደማመጥ የማይችሉ እንደጨረባ የሚንጫጩ አገራዊ እውነታንና ሐቁን እያውረገረጉ ሕዝቡ ቆርጦ እንዳይታገል የሚያደናግሩ ከኢትዮጵያውነት ይልቅ ፓን አፍሪካኒዝምን የሚሰብኩ የራሳቸው ወጥ ሲቃጠል የጎረቤት የሚያማስሉ እስከ ዛሬ የት ነበራችሁ? ቢባሉ ማጠፊያው የሚያጥራቸው ከሕዝባቸው ይልቅ ባዕድን ሙጢኛቸው ያደረጉ ናቸው።

 መጽሐፍ ፃፍን ቢሉ ማጣፈጫው ኢሕአፓን መኮነን ነው። በብዙሃን በሙያና በፖለቲካ ድርጅት መሃከል ያለውን ልዩነት እንኳን ለማጤን የማይተጉና የማይገነዘቡም ጋግርቶች ናቸው። ወደ ሕዝባዊው ጎራ ለምን መጣችሁ? አይደለም። ለመተያያና መተጫጫ ኢሕአፓን የእጅ መንሻ አታድርጉት እንጂ። የደርግ ኢሠፓ አባላትም ለምንስ በተቃዋሚው ጎራ ተሰለፋችሁ ? አይደለም። የተደራጃችሁበትን ድርጅት ራዕይ ማራመድ እንጂ የትላንት ባሕሪያችሁን ለማርካት ተቃዋሚ ድርጅቶችን ሽፋን ለማድረግ መሞከሩ ፋይዳ የሌለውና መዘዙም ብዙ ይሆናል ነው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ብቅ እያሉ ከስመዋል። ዛዲያ ለመፍረሳቸው አባላቱና ደጋፊዎቹ አለን የሚሉት ራዕይ እንጂ ማንም ተጠያቂ አይደለም። ከሞላ ጎደል የጨኸቱና የዘመቻው ምክንያትና የእሪ ባዩ ዓይነትና

ምንጭ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል። ይህ በግርድፉ ለማስቀመጥ ያህል እንጂ ዝርዝራቸውና ዓይነታቸው በየወገናቸው ቢተየብ ሆልቆ መሳፍርት ነው።

ሰሞኑን ደም የጠማው የውቃቢአቸው መንፈስ ተነስቶባቸው በኢሕአፓ ላይ የሚያጓሩት ማንንነታቸው እንግዳ ያልሆነ ከተራ ቁ.1 እስከ ተራ ቁ.4 በጠቅስናቸው አዝማችነት የሚንቀሳቀሱ የእነርሱም ውላጆች እንደሆኑ የሚታወቅ ነው። ለድፍን ሁለት ዓመታት ሕዝባዊ የትግል ጎራውን እየከፋፈሉ ሲያምሱ የቆዩ የወያኔ ኢህአዴግና የደርግ ኢሠፓ እንግዴ ልጆች ናቸው።

ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ቢሰፍንና ሕዝባዊ መንግሥት እውን ቢሆን ከተጠያቂነት አንድንም በሚል ተስፋ የቆረጡ ወደ አገራቸው የማይመለሱ ኢትዮጵያዊነት ከኛ በላይ ለአሳር እያሉ የሚገዘቱ በተግባር ሥራቸው ግን መከፋፈል መበታተን ማደናገር አሉባልታን ሥራዬ ብለው የተያያዙት እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል ያሉ ዛሬ ክበው ነገ መጣልን የተካኑ የአደንዛዥ እፅ ሱረት እየሳቡና እያነጠሱ የጫት ጌሾ ቅርሻታቸውን የሚተፉና ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉ ወያኔ ኢሕአዴግን ሳይሆን ትግሬዎችን የሚከሱ ጠባብ ብሔርተኞችን ሳይሆን ኦሮሞዎችን የሚገፉ ናቸው።

የዚህ መድረክ ታዳሚዎችና ቁልፉን የያዙት ቅንጅትንና ኢትዮጵያዊነትን ሽፋን አድርገው የሚንቀሳቀሱ የሠሩት ግፍ እንቅልፍ እየነሳቸውና እየባነኑ ዛሬም ኢሕአፓን የሚረግሙ የደርግ ኢሠፓ ነፍስ ገዳይ ለመሆናቸው የሚያጠራጥር አይደለም። ስርጭታቸውም በሰሜን አሜሪካ በአትላንታ በቦስተን በሳንሆሴ በዲሲ በቶሮንቶና በካልጋሪ በአውሮጳ ደግሞ በበርሊን በሙኒክ በአምስተርዳም በሎንዶን ስቶክሆልም በአውስትራሊያ በሲዲኒና በሚልቡርን እንደሆነ ይታወቃል። አስፈላጊ ሲሆን የስም ዝርዝራቸውን ማቅረብ ይቻላል።

ዝም የተባሉት በወደቀ ግንድ ምሳር ይበዛ እንዳይባል እንጂ ዝም ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን ትኩረቱ ወያኔ ኢህዴአግ ላይ በመሆኑ ነው። በሕይወት ያሉቱ ግፍ የተፈፀመባቸው ግፉዓን የኢሕአፓ ጋዶችም በእነዚሁ ከተሞች የሚኖሩ እንዳሉና እነዚህን ነፈስ በላዎች ባሉበት ወደ ሕግ ፊት ለማቅረብ በቂ የሰው የሠነድ ማስረጃና የሕግ ዕውቀትም አለ። የአልጋ ቁራኛው ፒኖቼት እንኳን በ90 ዓመቱ ከነአልጋው ሕግ ፊት እንደቀረበ ልናስታውሳቸው ተገቢ ይሆናል። እረ ለመሆኑ የኢሕአፓ ሰማዕታት ለፈሰሰው ደማቸው የሚቆረቆር ቢያንስ ቢያንስ ወላጅ እናትና አባት እህትና ወንድም አይኖራቸው ይሆን?

˜ኢሕአፓ እንቀፋት ሆነብን ተነካን ሌላ ጊዜም የኢህአዴግ ጦር ሶማሌን መውረር ደገፈ ኤ.ኤፍ.ዲን ተቃወመ ቅንጅትን ለማፍረስ ዶር ታዬ ወልደ ሰማዕትን አሠርጎ አስገባ ኢትዮ-ላይን ደብተራው አሲምባ...ወዘተ ድህረ ገፆች  ኢሕአፓዎች ናቸው።™ ይህን አወጡ ያን አወጡ እያሉ አልፎ ተርፎም የቅንጅትን አመራር ሳይቀር የሚያብጠለጥሉ በሱስ የተበከሉና

መሸተኞች ትዳራቸውን አላግባብና ያለ በቂ ምክንያት የበተኑ ሠርቶ እንደመብላት ለታሰሩት ለቅንጅት ለራዲዮ...ወዘተ በሚል የሰበሰቡትን የሱስ ማርኪአቸውና ማርክውሻቸው ያደረጉ ስድ አደጎች ለመሆናቸው ከአንደበታቸው ከሚወጣው ፀያፍና ልቅ ቃላት መገንዘብና መገመት ይቻላል።

ኤ.ኤፍ.ድም የውኃ ሽታ ሆኖ የቀረው ስብሰቡን ያማከለው በወያኔ ኢህአዴግ የሚደርስባቸው ግፍና ሰቆቃ የተነሳ ጥላቻ ብዛት እንጂ የጋራ ራዕይ የሌላቸው የመሆናቸው ገሃድ እውነት በመሆኑ ነው። የማንኛውም ሕብር ወይንም ትብብር ስኬት የሚለካው በገዢው ቡድን ላይ ባላቸው የጥላቻ ብዛትና መጠን ሳይሆን ባስተባበራቸውና ባማከላቸው ራዕይ ጥንካሬና እሴት ላይ ነው። ኤ.ኤፍ.ድ ቢፈርስ እንደ ቁምቡርስ ዓይን የሌለውና ራዕይም የጎደለው አቅጣጫውንም የማያውቅ የወያኔ ኢህአዴግና የሻዕቢያ መናጆ በመሆኑ ብቻ እንጂ በሌላ ኃይል አይደለም።

እስረኞች ይፈቱ ሲል ቀደም አድርጎ መግለጫ ያወጣው ሕብረት መሆኑ እየታወቀ ደርሶ የአዛኝ ቅቤ አንጓች በመሆን™ እስረኞቹ እንዳይፈቱ መሰናክል ሆኑ™ ሲሉ የእምዬን እከክ ወደ አብዬ ይለክካሉ። የእስረኞቹ ቤተሰቦችም ቢወተውቱ ሰሚ አላገኙም ነበር። ሰልፋን ቅንጅትም ይጥራው ሕብረት የወጡት ሕዝባዊ ወገኖችም እንደ ናዚዎቹ ስዋስቲካ ክንዳቸው ላይ ኢሕአፓ የሚል ምልክት ማሰር ካልነበረባቸው በስተቀረ ለታሰሩት ሁሉ ድምፃቸውን ከማሰማት የተዘናጉበት ጊዜ የለም። የኢሕአፓ መሪዎችና አባላቱ በአደባባይ ሲረሸኑና በእስር ሲንገላቱ ቢያንስ በኢ. ስ.መ.ጉ ዘገባ እንኳን ዝርዝራቸው ሊወጣ ባለመቻሉ አቂመውም የታሰሩት ሁሉ ይፈቱ ከማለት አልታቀቡም። የሳሊና እስረኞችንም በፖለቲካ አመለካከታቸው የሚፈርጅ አንጀትም የላቸውም። ˜ማፈር ድሮ ቀረ™ ሆነና ሊያፍር የሚገባው ማን ይሆን? ማፈር ድሮ ምቅረቱን የተረዳነው ገና ጋሜ ሳለን ከተዘርፉት ቅኔዎች

የልጃገረድ ከርታታ

አውራ መንገድ ላይ ተኝታ

ተነሺ ቢሉዋት ምነው

ይህ ሁሉ አለማፈር ነው

ከሚለው ስንኝ ሰማና ወርቁን ለዩ ስንባል ነበር። ወርቁ አለም አፈር መሆኑን ለይተንም በተራበ ሕዝብ ዘንዳ ጠግበን ለማግሳት በታረዘም ወገን ዘንዳ ደምቀን ለመታዬት ሳንጓጓ ሀብት ንብረትና ምቾትን ንቀን ቢቀናን እምባውን እናብስ ዘንዳም እየተጋን አለን። ዛዲያ የታሰሩት ሁሉ ይፈቱ ተብሎ ሰላማዊ ሰልፍና የሻማ መብራት ሲጠራ በብርዱ እያመካኙ ጭር ያሰኙት

እነርሱ ከመሆናቸውም በላይ ˜ምንም አይሆኑ እነርሱ እኮ ያጡት ነገር የለም። የገንዘብ ችግር የለባቸውም። እገሌ የዶሮ ርባታ አለው እገሌ ባለቤቱ ክሊኒክ አላት እነ እገሌ ደኅስ ያለ ጡረታና ሮያሊቲ ያላቸው ናቸው™ እያሉ ንዋያቸውንና ገቢያቸውን ቃሊቲ ተቀምጠው እንዲበሉ ሲፈርዱባቸው አላፈሩም። ˜ከቃሊቲ የሚመጣ ደብዳቤ አንቀበልም™ እያሉ ውዥንብር ሲነዙ መሪዎቹ ድንገት በመፈታተቻው መግቢያው የጠፋቸው ዓይናቸውን በጨው ያጠቡ ነጭ ውሸተኞችና ፍርሃት ያረበባቸው በሽተኞች (pathological liars and clinical level oaranoids) ናቸው።

ኢ.ኤፍ.ዲ ‡ኢ.ኤፍ.ዲ እያሉ ከበሮ እንዳልደለቁ ያህል በኦሮሞ ኒክ ኔም የሚገቡ ታዳሚዎችን በምንችለው ቋንቋ እንናገር አማርኛ ይከብደናል ያሉትን ማዋከብ በቀይ ማስወጣት ኦሮሞዎችን መግፋት ተግባራቸው አድርገው ይንቀሳቀሳሉ። ሐጎስ በሚል ኒክ ኔም የገባን የቅንጅት ደጋፊ ታዳሚን በስሙ ንትርክ ፈጥሮ (አንድ ጊዜም ትንሳኤ ራዲዮ ቀርቦ የነበረ ) ስምህን ካልቀየርክ ተብሎ መዋከቡ እጅጉን አሳፋሪ ከመሆኑ በላይ ምን ያህልና በተቻላቸው መጠን ሕዝባዊ ኃይሎች ወደ አንድነት ጎራው እንዳይጠጉ የሚከላከሉ የወያኔና ሻዕቢያ ዕቅድ ከዋኞች ናቸው። ፀረ ወያኔ ኢህአዴግ ሳይሆኑ ትግሬ ጠል ናቸው።

ብዙውን ጊዜ የሚበሳጩት ወያኔ ኢህአዴግና ደርግ ኢሠፓ በሠሩትና በሚሠሩት እኩይ ተግባር ፀፀትን የማያውቁ የአዕምሮ በሽተኞች ናቸው እየተባለ በሎቢው ላይ ሲፃፍ አረፋ መድፈቅ ይጀምራሉ። ደርግና ወያኔን እንዴት አንድ ታደርጋላችሁ? ይላሉ። ቀልቀሎና ስልቻ ያው ቆዳ መሆኑን አይረዱም ወይንም እግሞ ይክዳሉ። አንዱ ይህን የሚሉት ኢሕአፓዎች ናቸው ሲል ሌሎችም ቀበል አድርገው ˜ኢሕአፓ አለ እንዴ?™ ወይም ደግሞ ˜ሞቷል™ ይላሉ። አዎን ተሰውተናል ደማችን ፈሳል አጥንታችን ተሰብራል አካላችን ጎድላል ብንል ውሸት አይደለም ።

ይህ ሐቅ ለመሆኑ ከመሪዎቻቸው ግልፅ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ዶር ያዓቆብ ኃይለ ማርያም ገፅ ሦስት ተ. ቁ. ሸ. ይጠቅሱዋል። ‡˜በቀይ ሽብር ጊዜ በጉራጌ ዞን በቸሃ ወረዳ በጉብርያ ትምህርት ቤት አንድ እናት በተገደለው ልጅዋ ሬሳ ላይ ሕዝብ እንዲረጋገጥበት ሆኖ የልጅዋ አንገት ተቆርጦ ያንን የልጅ ጭንቅላት ተቆርጦ ያንን የልጅ ጭንቅላት ሠርቃ በጉያዋ ሸጉጣ ስትሮጥ ያየነው ከሕሊናችን አልጠፋም ስላለንና እንዲህ ዓይነት ነገር በአገራችን እንዳይደገም በማሰብ ነው™ ሲሉ አስነብበውናል። በለስ ቀንቶን ጉዳታችንን ለፍትህ አንድ ቀን ማቅረብ ብንችል እማኝ ብለን መቁጠር እንችል ይሆን? አደራ በሕግና ወድቃ በተነሳቺው ባንዲራ ይሁንና ˜የፍትህ ንግስትስ™ ትፈርድልን ወይንስ ትፈርድብን ይሆን?

መሪዎቻቸው የሚሉትንም የማያውቁ ወይንም ደግሞ ፈፅሞ ለመስማት የማይፈለጉ የግለሰቦችን ስም ማጥፋት ሥራቸው ያደረጉ ስድ አደጎች ናቸው። የዳፍንትና የፍናፍንት መንፈሳቸውም እየረባሻቸው ኢሕአፓን በታኝ ነው ይላሉ። ወደ ቅንጅትም ዶር ታዬ ወልደ ሰማዕትን አሰርጎ

አስገባ ሲሉ ዶር ታዬንና ኢሕአፓን ይከሳሉ። ዶር ታዬ ባልዋለበት ተሰድቦአል ። ነገር ግን ዶር ታዬ በማንኛውም ረገድ የሚታማ ሰብዕና ያለው ሰው ካለመሆኑም በላይ ስድስት ዓመት በሠንሠለት ታስሮ ፍዳውን ያየ ጀግና ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ እማኝ አይሻም። የፖለቲካ ዝንባሌው የግለሰብ ነፃነቱ ነው።

የግለሰቦችን ስም ማጥፋት በዶር ታዬ አላበቃም። በቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራርና በሻለቃ ዮሴፍ ያዘው መካከል ተፈጠረ በተባለ ውዝግብ ከቃሊቲ መጣ በተባለ ደብዳቤ ላይ በተካሄደ ውይይት አታካሮ እንጂነር ኃይሉ ሻውል ዓይናቸውን በጠና ታመዋል ሕክምና ያስፈልጋቸዋል በሚባልበት ሰሞን ™ከቃሊቲ የመጣ ደብዳቤ አንቀበልም ኃይሉ ሻውል በምን ዓይኑ አይቶ ነው የሚፈርመው በአንድ ሰው የተፈረመ ደብዳቤ አንቀበልም ይኼማ አምባገነንነት ነው ማኒፌስቶውን መቃወም ነው™ ሲሉ በአግራሞት ታዝበናል። መሪውን እንዲህ የሚያብጠለጥል ደጋፊ ከበስተርጀባው የሚገፋው አንድ ኃይል እንዳለ መገንዘብ አዳጋች አይደለም። በእስር ላይ ያለን መሪ ታግሎ ማስፈታት ቢያቅት ቢያንስ እግዜር የፍታህና ይማርህ ኢትዮጵያዊ ርህራሄና ባህል ነበር። የመሪነቱ ክብር ቀረ? ቆላ ደጋ ወርዶ ማደራጀቱስ ተረሳ? በሙያው አገሩን ሲያገለግል ለደረሰበት የዓይኑ ጉዳትም ወሮታ ይህ ባልሆነ ።

እንስት ታዳሚዎችን ማዋከብ ፀያፍ መስደብ የተዘወተረ ነው። ተበደልኩ ባዩ ሴትም የበዛ ነው። ወያኔ አዲስ አባባ ሲገባ የአንድ ቀን አራስና ሕፃን ጥላችሁ ከሸሻችሁቱ የደርግ ኢሠፓ ቡከናም ነፈሰ ገዳዮች እንደበት ከጀርባቸውም ሆናችሁ ከምትነዱአቸው ከሀዲ የሥልጣን ጥመኞች ገና ብዙ ክፍፍልና ክህደት እንጂ የሴቶችን እምባ የሚያብስ ምንድን ፋይዳ ይገኛል?

ከቃሊቲ ተላኩ ከሚባሉት ደብዳቤዎች መሃከል በየድህረ ገፁ ከሚወጡት አንዱን ለዩት የሚያደርገው ከአንድ እስረኛ ሌላውን እስረኛ ዶር ብርሃሁ ነጋን እጅጉን በማድነቅ የፃፈውና ይህንኑ እስረኛ ብፁዕ ወቅዱስ አሳሪዎቹን አፍቃሪና ወዳጅ አድርጎ ለንባብ ማብቃቱ ሌሎቹን እስረኞች ትምክህተኛነት አምባገነንነት ለማሳዬት እስረኞቹንም ለመከፋፈል ሴራ እንዳለ ጠቃሚ ፍንጭ ነበር። ዛሬም ይኸው እንደቀጠለ ነው። ዬት ይደርስ ይሆን?

ዛሬ በዚሁ መደረክ የኢሕአፓ አመራሩ ማነው? የቅንጅት ዓይነት መዋቅር አለው ወይ? የአመራር ምርጫ አካሂደው ያውቃሉ ወይ? ጥያቄዎችም ተዘወትረዋል። ዛዲያ የዚህ ሣር አጨዳው ዱባ ፍለጋ ነው። የጥያቄው መልዕክት ሀገር በቀልና የውጭ ጠላት ስለ ድርጅቱ እንቀስቃሴ በቂ መረጃ አላገኘም። ወይንም ደግሞ የኢሕአፓ እንቅስቃሴም አስግቶታል ማለት ነው። ይህም በወገን ላይ የሚደረግ የሰላይ ተሰላይ ደባና ሸር ነው። አሊያም ባዕድ ቢችል ኢህአዴግን በሥልጣን ለማቆዬት ወይንም ደግሞ ለመተካት የሚያደርገው ዝግጅትና ጥረት እንቅፋት የሚሆኑትን ወይንም ናቸው የሚላቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገኖችና ዴሞክራሱያዊ

ኃይሎችን ለማግለልና ለማስጠላት የሚደረግ የዘመቻ አካል ነው። ሁሌም በአገርና በሕዝብ ጥቅም ላይ መደራደር በጀ የማይለው ኢሕአፓ ነውና ሊገርመን አይገባም።

˜በቅንጅት ማኔፌስቶ ገብተው ቢታገሉ ይሻላል™ የሚል ምክር ቢጤም አድምጠናል። አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ፃፍኩ የሚሉት ማኒፌስቶ ከሆነ አቶ አንዳርጋቸውንም ሆነ ዶር ብርሃኑ ን ቃሉን ያስተማራቸው ማን ሆነና። ዛሬ ደርሰው ፃፍነው የሚሉት ለስሙዋ መጠሪያ ቁና ሰፋች ˜አማራ ከዬት ወደ ዬት™ ርሚን ብታፈላ ኃን ሙሉ አተላ ነው። በጊዜው በ1983 ዓ.ም ይዘቱን ለጠየቁን የትላንት ደቂቃን የዛሬ ጎልማሳዎች ይህ ሰው የወያኔ ቡሃቃ ለሁለት ዓመት ያህል ተሸካሚ የነበረና ከፍ ያለ ሥልጣን ቢቋምጥም ወያኔ ችላ ያለው የጋገረውም የሁለት ዓመት የወያኔ ቡኮ ነው ብለን ያለፍነው ነበር። ዛሬ ደግሞ ማኔፊስቶ ፃፍኩ ሲሉን ምንድን ብንል ይበጅ ይሆን? ማኒፌስቶ ዴሞክራሲያ‡ ወዘተ ቃላትን አሃዱ ብለው የሰሙት ከኢሕአፓ ዘንዳ መስሎን። የፖለቲካ ገንፎ ከፓልቶከኞች ተርፎ ብሎ ማለፉ ይበጃል።

የዶር ብርሃኑ ነጋም ˜ጎህ ሲቀድ መነበብ ያለበት™ መጽሐፍም የኢትዮጵያን ሕዝብ የፖለቲካ ገሃድና የኃይል ሚዛን ያልተነተነ ጠላትና ወዳጅ ያልለዬ እንቶ ፈንቶ የጭንቀትና የፍርሃት ማስታገሻ ቡቱቶና የቃሊቲ ወህኒ ድሪቶ ነው። ላም ጥቁር ወተት ትታለባለች ዶሮም ጥርስ ታወጣለች ቅዠትና የቀን ሕልም ነው።

የኢሕአፓ ሰማዕታትንም በተመለከተ ስህተት ነበር የአንጃና ከሃዲዎች ቅዠት እንደ አቶ አሰፋ ጨቦ ™አላርፍ ያለችጣት‡ ˜ ዓይነት የአዕምሮ በሽተኞች ስላቅም ተደምጣል። ሐቁ ግን ቀድሞ መሰዋት የጀመረው የኢሕአፓ አመራሩ እንደነበር መጥቀሱ አስፈላጊ ነው። አመራሩ እየተሰዋ አርዓያ ሆነ አባላቶቹም ፈለጉን ተከተሉት እንጂ ። ዶር ተሰፋዬ ደበሳይን ሥዩም ከበደን ግርማቸው ለማን መምህር በላይን ኢንጂኔር ኡስማንን‡ ወዘተ ከቀደምት ሰማዕታት መጥቀስ ይቻላል። ገድላችና ሞታችን ከቋጥኝ የከበደ እንጂ እንደ ባንዳዎቹ ከዶሮ ላባ የቀለለ አልነበረም። ወደፊትም አይሆንም ። ተጠያቂዎቹም ደርግ ኢሰፓና ወያኔ ኢህአዴግ አንጃዎችና ከሃዲዎች ናቸው።

ከስደት ፖለቲካ የሚገርመው የድጋፍ ነን የሚሉ በተቃዋሚዎች ፕሮግራምና ስልት ላይ አቃቂር እያወጡ ˜አመራሩ ሊነገረው ይገባል እኛ ማወቅ አለብን™ ማለታቸው በዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ የፖለቲካ ድርጅት አባላት ያልሆኑ ደጋፊዎች የትግል ስልት ለመንደፍ ሲጥሩ የታየው በኢትዮጵያ የሰደት ፖለቲካ ውስጥ ነው። ይኸም ትልቅ ግኝት ሆኖ በዓለም የፖለቲካ ፓርቲዎች ታሪክ ሳይመዘገብ ይቀር ይሆን? እረ ለመሆኑ ሰምበቴና እቁብ እንኳን መተዳደሪያ ደምቡን ለመቀየር የማህበሩ አባል መሆንን አይጠይቅ ይሆን?

ከምርጫው በፊትና በኃላም በየድህረ ገፁ በተከታታይ ከዚህ ቻፕተር ከዚያ ቻፕተር እየተባለ በአብዛኛው ይወጡ የነበሩ ፅሁፎችን በውል ላጤነ የተቃሚዎች ድርጅት አለት በየቻፕተሩ

ከተሞች የመሸገ አስመስሎታል። የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችም ቦታና ጊዜአቸውን አገናዝበው አተሻለና ፋይዳ ያለው ውሳኔ ላይ እንዳይደርሱ ከፍተኛ ተፅእኖ ሳያደርግባቸው እንዳልቀረ ይገመታል። አስተያየት ከሆነ መልካም ነበር። በድህረ ገጽና በፓል ቶክ ሳይሆን በአደባባይ ማዝረክረኩ ኃላፊነት የጎደለውና አፍራሽ ከመሆኑ ባሻገር የሚቀጥለውን ርምጃ ለጠላት በመጠቆም ጠላትም ምን ሊመጣ ይችላል? ብሎ ሳይጨነቅ ጠቃሚ መረጃ እንዲያገኝ የረዳና ዛሬም የሚረዳ ነው።

በ2005 ዓም ምርጫ ማግስትም ተቃዋሚዎች ሲዋከቡ በዚሁ የፓል ቶክ መድረክ ሁኔታቸውን እናጣራ በሚል ዞግ በአጋፋሪው የኢትዮጲያን ሪቪው ኢዲተር አቶ ኤልያስ ክፍሌ አማካይነት ታዳሚው ˜የ$5 የሰልክ ካርድ አምጡ™ እየተባለ የኢትዮጵያ ነገር የማይሆንለት ታዳሚም የተባለውን የስልክ ካርድ እየለከ በስልክ ውጊያውም የተደወለላቸው በሙሉ ቃሊቲ ወርደዋል። ይህም አጋጣሚ ይሁን ወይንስ ምንድን እስከ ዛሬ አባ ካና ያለው የለም።

አንድ ውክልና የተሰጠው አካል የኃላፊነት ገደብና የሥራ ዝርዝር ቢኖረውም የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር በኢኤፍዲ ምስረታ ተሳትፎ የአመራሩን ይሁንታ ማግኘት አለማግኘት እስከ ዛረ በገሃድ የታወቀ ነገር ባይኖርም በሰላማዊ መንገድ ለሚታግል ድርጅት ለዚያውም ጉምቱ የአለት አካላቱ በጅምላ ወህኒ በወረዱበት ሰዓት የኢ.ኤፍ.ዲ ስምምነት ኃላፊነት የጎደለውና መሪዎቹም አራት እግራቸውን ይብሉ ያለ እኩይ ተግባርና ቀድሞም ጊዜ ቦታና አጋጣሚን ሲጠብቅ የነበረ አድርባይነትና የሥልጣን ጥመኝነት ብቻ ነው።

ሕዝብ ያከበረውን ሊያዋርድ የሚችል ምንም ኃይል የለም። ሕዝቡም ተከተለኝ ያለውን ሁሉ ሆ ብሎ የሚከተል አለመሆኑን አለመገንዘብ ራዕይ አይተንልህ የሚሉትን ሕዝብም መናቅ ነው። ለራሱ ሳይማር ያለማንምና ያለምንም ድጋፍ (family guidance and child support) ይህን ሆልቆ መሳፍርት ዶርና ፕሮፌሰር ለወግ ያበቃ ሕዝብ ሊደነቅና ሊመሰገን ባይታደል እንካን ባይናቅ ምን አለበት?

ሲሉ ሰምታ ዶሮ ተጤስ ገብታ እንዲሉ ግድ ሆነና የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ለጠራውና ከዲሲ ለጎሰመው ነጋሪት ከተማ ጭር የማድረግ አድማ መልሱ ዝምታና ጆሮ ዳባ ልበስ መሆኑ ይህቺም ከተማ ሆነችና ቂጢኝ አፈራች ነው። አመራር ሌላ ሕዝብ ሌላ ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ የተባለው ቀልድ ቢጤ መሆኑ ነው። ዛዲያ ይህ በየፊናው በየፖለቲካ ወገናችን ለተሰማራነው ትምህርት ሊሆነን ይገባል። ሕዝቡ ቀድሞ እየጠበቀን ተቃዋሚዎች ከኃላ እያነከስን መከተሉ የፖለቲካ ጭራነት ነው። የሕዝቡንም ስነ-ልቡናና የትግል መንፈስም ሰላቢ ነው።

መቼም መንፈስ ሲባል ወዲያው በአዓምሮአችን ጋዳ እንደ ጉሽ ጠላ መፍላት የሚጀምረው የእምነት ጉዳይ ነው። የመንፈስ ነገር ሲነሳ ርኩስ መንፈስ ውቃቢ አዶ ከብሬ ዳፍንት

ፍናፍንት የማይድን ደዌ ቅዱስ መንፈስ ደግሞ ፍቅር ርህራሄ ደግነትና ምህረት ይታሰቡናል። ዛዲያ መንፈስ ስንባል ዬትኛው? ብለን ማጠየቃችን አይቀርም። ባለ ውቃቢ ደብተራና ሼካ ሥር ማሽ እንደ መድሃኒት አዋቂም ይቆጠራል።

አንዴ እግር ጥሎኝ ከነኣዳዴ መንደር ብደርስ ኣዳዴና ጃላዋ ስለ አንድ መድሐኃኒት ዓዋቂ ሼካ ያወራሉ። ጃላዋ ዛዲያ ተጠንቅቃና ቃላት መርጣ "ጋናማ ጋናማ ሱጲ ካኢት ካናፊ ካና ጎሪ ናጀናን እቲን ጂራ" ትላታለች። ታዲያ የዚሁኑ ሼካ የማዳን ችሎታ የምትጠራጠር ኣዳዴ እንዲህ ትላለች "እሲኒ ማሊፍ ሼካ ሼካ ጀቱ ሲላ ሼካን ኩኒ አላቲ ቡሳ? ሼክን ኩኒ አላቲ ቡስናን ኢት ኣማና" ትላታለች። ድፍረቱዋ የገረመኝ መንፈስና ውቃቢ ሲባል ይፈራልና ነው። ይኼ በየፓልቶኩ መንፈስ መንፈስ የሚባለው ታዲያ መንዙማም ተገጥሞለታል። መንዙማ የሚያምረው በረመዳን ከነኣዳዴ ቤት ነበር፡፡ ያለ ወቅቱና ያለቦታው ሲሆን ማሾፊያና መሳለቂያ እንጂ መወደሱ ለተገጠመለት ዱኣኢውም ለተለመነለት ሰብዕም የትግል ስንቅ አይሆነውም። በስተርጅና ራፐም ተዘፍኖለታል ። "ማፈር ድሮ ቀረ።" ግና ደግሞ ይህን የዴሞክራሲ መንፈስ አሞራ በላያችን አውርዶ የሚገላግለን ማን ይሆን?

ሕዝቡ አንድ ነገር ጠንቅቆ ያውቃል ኢሕአፓ መንፈስ አይደለም። ሕልው የሆኑ የሰብዕ ፍጡራን በሃብት በዕውቀት በዘር በሃይማኖትና በፆታ ሳይለያዩ ለአንድ ሀገር ምልዓተ ሕዝብ በተለይም ምንዱባንን መሰረትና ተገን አድርገው የታገሉበትና የሚታገሉበት በኩር የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅት እንጂ። ምንዱባንን ለመታደግ እምባቸውንም ለማበስ ዛሬም አበክረን እንታገላለን ። ክርክራችንም እንደ ነሐስ የሚጮህ እንደ ፀናፅልም የሚንሹዋሸዋ ከንቱና ብኩን አይደለም። በጨረባ ጨኸትም አይበሳጭም። አይፈርስምም።ስለ ግፍ ደስ አይለውም። ከሕዝብና ከሐቅ ጋር በፅናት መቆምን እንጂ።

ባለፈው ሠላሳ ዓመት ምንድን ሠሩ? ምንድንስ አመጡ? ጥያቄዎችም የጩኸቱ ምሶሶና ማገር ናቸው። ማጣጣል? ዛሬ በሁለት ዓመት የተገኘው "ድል" ና የፖለቲካ ለውጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ብቁና ዝግጁ መሆኑን ማሳዬት መቻሉ የሠላሳ ዓመታት የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ትግል ጥረት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ካልሆነ በስተቀረ። እንግዲህ መንፈሱ አልበጀ ውቃቢው ሰው ፈጀ ብሎ አገር በቀልና ባዕድ ጠላት እንዳይዘባበትብን ኢሕአፓን ለቀቅ ወገባችንን ጠበቅ ማድረጉ ይበጃል። ለአንድ ድርጅት ብቻ ሳይሆን ለዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ ጥንካሬ ለአገርም መድህን መሆኑን መገንዘብም ያሻል። የአንድነት ኃይሎችም እየገዘፉ እንዲመጡም ዕለት ዕለት መትጋት አስፈላጊ ነው። ጃርት የበላው ዱባ እስክንመስል መተፋተፉ የወገናችንን የሰቆቃ ዘመን ከማራዘም በስተቀር የሚፈይደው አንዳች ነገር የለም። ዛሬም ዕድሜ ለምልዓተ ሕዝቡ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

**ኢሕአፓ ያቸንፋል!!**